Email: contact@shegasab.com
Land line: +251 115 57 97 57
Mobile: +251 980 37 38 39



Shegasab

Shegasab Training and Consultancy PLC

**አለም አቀፍ ፓተንት አለ?**

**አለም አቀፍ ፓተንት (International Patent) እንዴት ማግኘት እችላለሁ?**

ብዙ ጊዜ አለም አቀፍ ፓተንት ሲባል ሰምተን ሊሆን ይችላል። ይህ ግን በመርህ ደረጃ ትክክል (Theoretically applicable if the inventor registers its invention in all countries) በተግባር ግን ትክክል ያልሆነ (Practically Impossible) አባባል ነው።

**ለምን?**

እንደ ፓተንት (Patent)፣ ዲዛይን(Design)፣ ግልጋሎት ሞዴል(Utility Model)፣ የንግድ ምልክት(Trademark) እና መሰል መብቶች በባህሪያቸው ድንበርተኛ (Territorial) መብቶች ናቸው። እዚህ ጋር ፓተንት ጥበቃ ለማግኘት አለም አቀፍ የአዲስነት ምርመራ (Novelty search) ይደረግለታል ማለት የምናገኘው መብት አለም አቀፍ ነው ማለት አይደለም።

ስለዚህ አለም አቀፍ ፓተንት የሚባል መብት የለም። ነገር ግን አለም አቀፍ የፓተንት ማመልከቻ ሂደት አለ። እሱም ፓተንት ኮፐሬሽን ትሪቲ መንገድ (PCT Route) ይባላል። በዚህ መንገድ በአንድ ጊዜ አለም አቀፍ ማመልከቻ ካስገባን ብኋላ የተለያዩ ሂደቶችን እያለፈ ለ30 ወራት ይቆያል። ከ30 ወራት በኋላ ግን ተመልሶ የፈጠራው ባለቤት የመረጣቸው ሃገሮች (National Phase) ጋር መመዝገብ አለበት።

**ይህ ምን ማለት ነው?**

ለምሳሌ አንድ ግለሰብ ኢትዮጵያ ውስጥ የፈጠራ መስፈረቱን አሟልቶ ፓተንት ቢያስመዘግብ ጥበቃ የሚደረግለት ኢትዮጵያ ውስጥ ብቻ ነው። በሌሎች ሃገሮች ተመሳሳይ ጥበቃ ከፈለገ ወይ በቀጥታ በመረጣቸው ሃገሮች (Direct/Paris route) ወይም አለም አቀፍ የማመልከቻ መንገድ (PCT rout) መከተል ይኖርብታል።

*ስለ ፓተንት ወይም ሌላ ጥያቄ ካለዎት ወይም የበለጠ ለማወቅ ከፈለጉ በየሳምንቱ የነጻ ጥያቄ እና መለስ ፕሮግራማችንን ወይም በትሬኒንግ ውስጥ ከተዘረዘሩ ስልጠናዎች መካከል መርጠው ይመዝገቡ። ወይም ኮንታክትን በመንካት ያግኙን!*

© [2025] Shegasab. All Rights Reserved. The unauthorized reproduction, distribution, or transmission of this text is strictly prohibited and subject to legal action under applicable copyright law.